# ሚዛኑ እንዴት ይጥፋ?

የልጅነት ዘመን ፣ ያብሮነት ማደጉ
አለሁልህ ማለት ፣ ለክፉም ለደጉ
በቃል ፣ ጸንቶ መቆም ፣ ክብርና ማዕረጉ
ዘመን አረጀና ፣ ተሻረ ወይ ፣ ወጉ?

አብረው የለፉበት ፣ መውጣቱ መውረዱ
ጠመዝማዛነቱ ፣ ተረስቶ መንገዱ
ሳይጨርሱ ጉዞ ፣ ከመንገድ መውረዱ
የራስ ፣ መድከም ሳያንስ ፣ ጓደኛን ማጥመዱ
ጠልፎ ለመጣያ ፣ መሽረብ መግመዱ
እንደ አህያ ስጋ ፣ ከብለል ፣ ወደ አመዱ
ማንን ፣ ለመጥቀም ነው ፣ በደም መነገዱ?

ጠላት አዘጋጅቶ ፣ ዘርግቶ ወጥመዱን
ሸርሽሮ እየገባ ፣ ሳይዘጉ መንገዱን
መለየት ተስኖ ፣ የጠላት ምንጭ ፣ ግንዱን
ስርዓት ፣ ባጣ መልክ ፣ ዝም ብሎ ፣ መንጎዱን
ወዳጅ ፣ በወዳጁ ፣ ጀምሯል መፍረዱን
እራስን ለመቅበር ፣ መቆፈር ጉድጓዱን ።

ባሉባልታ አንቀልባ ፣ ነገር እያዘሉ
ወሬ አመላላሾች ፣ የሚንዘላዘሉ
ወዳጅ መስሎ ፣ ጠላት ፣ እንዳሸን የፈሉ
እንዴት በደካሞች ፣ አይኑ ይጥፋ ፣ ትግሉ
መንሸራተት ሆነ ፣ የሰው ፣ ሁሉ አመሉ ።

ሰው ፣ እራሱን ሊገል ፣ እራሱን ሊያጠፋ
እራሱን ለማውደም ፣ ሲደክም ሲለፋ
መቃብሩን ሲምስ ፣ እራሱ ሲገፋ
በራሱ ላይ ፣ ማውራት ፣ በራሱ ልፈፋ
በራሱ ላይ ፣ ዋሽቶ ፣ በራሱ ልጠፋ
እራሱን ማንጓጠጥ ፣ እራሱን ውረፋ
እራሱን ማዋረድ ፣ እራሱን ለከፋ
ለቁም ነገር ፣ ሳይሆን ፣ ለጥፋት ቅልጠፋ
ህሊና ሲሻግት ፣ ማስተዋል ሲጠፋ
ሰው እራሱን ፣ ንቆ ፣ እራሱን ከተፋ
ከዚህ የበለጠ ፣ ምናለ የከፋ ?
ወርቁ እንኳ ቢጠፋ ፣ ሚዛኑ እንዴት ይጥፋ ?

ታዛቢው ... November 19, 2010